# አኮቴተ ድምፃውያን

እንግዲህ ሙዚቃ ምን ትል ይሆን
ተሰናብቷት ሲሄድ ልጇ ጥላሁን።
ትላንትና ካሳ እዩኤል ሚኒሊክ
እምታገኝ አይመስል እንደነሱእሚያመልክ።
እየለዋወጡ የሙዚቃን መልክ
ነበሩ ሐዋርያት የሙዚቃ መላክ።

በመሳጭ ቀረርቶ በጥዑም ዜማዎች
ባዘን በእንጉርጉሮ በሰርግ ዘፈኖች።
ባንቺ ሆዬ ዜማ በብርቱካኔ ነሽ
በባቲና ፋኖ በእንቆቅልሽ።

ይርጋ ዱባለና ለማ ገ/ሕይወት አበበ ተስማ
የሚያቀንቅኑት በዘለሰኛና በወዳጄ ዜማ።
አያልነሽ ፍቅርተ ጌጡና መንበረ
በቲያትር ሙዚቃ ቀድሞ የነበረ።
መልካሙ ተበጀ ሀብታሙ ሽፈራው
ሙዚቃ ሲጋጋል ቀድሞ የነበረው።

ወሰኑና አሊ እሳቱ ተሰማን
ባህሩ ቃኜና ከተማ መኮንን
ጌታ መሳይና ደርባባው አቡን
ታላቁን ዚቀኛ ያ ፍሬው ሀይሉን።

አሉ እነ አመልማል ደሞ እነ አለምፀሐይ
በዛወርቅ አስፋው ደሞ እነ ንዋይ
መና አልቀረንም ተርፏዋል ለአዋይ።
አስናቀች ወርቁና አስለፈች አሸኔ
ሙናዬ መንበሩ ትዝታ ወገኔ።

አሉ እነ ዘነበ እረ እነ ሙላቱ
አስቴር እና ፀሐይ ከዛሬም ከጥንቱ
መች ይረሳል በኛ ተሾመ ምትኩ
አለ እውስጣችን አይቀርም በከንቱ
ያለፉትም ሆነ በሕይወት ያሉቱ።

ማን ይረሳቸዋል እነ አሰፋ አባትን
ሸሸግ ቸኮልና ዘራፌ ንጋቷን
ሲሳይ ገሠሠና መስፍን ከበደን
ወጋየሁ ድግነቱ መራዊ ዮሐንስን
ብዙነሽ በቀለ ደሞም ሂሩትን
ታደለ በቀለ አያሌው መስፍን
ዓለማየሁ እሸቴ እነ ሙሉ ቀንን።

ተዘራ ሀ/ሚካኤል ያ ተፈራ ካሳ
ባንድ አይቀር ማስተዋስ አንድ አንዳይረሳ።

ክንፈ ሚካኤል
ሜልበርን፣ አውስትራሊያ
ግንቦት ፮ ቀን ፪ ሺህ ፭ ዓ/ም